የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.43
ADDIS ABABA, 5th June, 2017

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፲/፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በደን ልማት፣ጥበቃና ቁጥጥር ዙሪያ ለመተባበር የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ..................ገፅ ፱ሺ፮፻፶፯

**CONTENT**

PROCLAMATION NO. 1010 /2017

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Sudan on Forest Development, Protection and Inspection Ratification Proclamation ……………………………………………page 9657

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፲/፪ሺ፱

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በደን ልማት፣ጥበቃና ቁጥጥር ዙሪያ ለመተባበር የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ሚያዚያ ፲፬ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም በደን ልማት፣ጥበቃና ቁጥጥር የትብብር ስምምነት በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፲፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩)እና(፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል:-

## PROCLAMATION NO. 1010/2017

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUPBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUPBLIC OF SUDAN ON FOREST DEVELOPMENT,PROTECTION AND INSPECTION**

**WHERE AS,** the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Sudan on Forest Development, Protection and inspection was signed in Addis Ababa on the 22nd day of April 2009;

**WHERE AS,** the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its session held on the 23rd day of May 2017,

**NOW THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

፱ሺ፮፻፶፰

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በደን ልማት፣ጥበቃና ቁጥጥር ዙሪያ ለመተባበር የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፲/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. ስምምነቱ ስለመፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ሚያዚያ ፯ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በደን ልማት፣ጥበቃና ቁጥጥር ዙሪያ ለመተባበር በአዲስ አበባ የተፈረመው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. አስፈፃሚ አካል

ይህን ስምምነት እንዲያስፈፅም የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንበረት ለውጥ ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This proclamation may be cited as the "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Sudan on Forest Development, Protection and Inspection Ratification Proclamation No.1010/2017."

## 2. Ratification of the Agreement

The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Sudan on Forest Development, Protection and Inspection signed in Addis Ababa on the 22nd day April 2009 hereby ratified.

## 3. Implementing Organ

The Ministry of Environment, Forest and Climate change is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of this agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 5th day of June 2017**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**